# ትንቢተ ሐጌ-27

## ጥናት አንድ (ሐጌ 1፡1-6)

የጥናት ዓላማ፡ የእግዚአብሄርን ቤት ችላ ብሎ በራስ ቤት ላይ ብቻ ማተኮር በኑሯችን ላይ ሊመጣ የሚችለውን የእግዚአብሄር በረከት ሊያግድ እንደሚችል ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡ ‹‹እስቲ መንገዳችሁን ልብ በሉ፤ ብዙ ዘራችሁ ነገር ግን ያጨዳችሁት ጥቂት ነው፤ በላችሁ ግን አልጠገባችሁም፤ ለበሳችሁ ግን አልሞቃችሁም…›› ሐጌ 1፡5-6

1. ሐጌ 1፡1-6 በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ1 መሰረት ትንቢት ተናጋሪው ማነው? የተናገረበት ዘመንስ መቼ ነበረ? ትንቢቱን የተናገረው ለማን ነው?
2. ‹‹ይህ ህዝብ›› በማለት በቁ2 ላይ የሚናገረው ስለማን ነው? ከዚህ ቁጥር እንደሚታየው፣ እነዚህ ሰዎች የእግዚአብሄርን ቤት መስራት አያስፈልግም ብለዋል ወይ? አስረዳ፡፡
3. ‹‹የእግዚአብሄር ቤት የሚሰራበት ጊዜ ገና ነው›› ማለታቸው ምን ማለት ይመስልሃል? በህይወትህ የእግዚአብሄርን ሥራ ለመስራት ጊዜው መልሎ የማይታይህ ጊዜ አለ ወይ?
4. በቁ2 ላይ ሰዎቹ የሚሰጡት ምክንያት ያተኮሩበትና እግዚአብሄር ጥያቄ ያቀረበበት አንደ ተመሳሳይ ቃል አለ፡፡ ይህ ሁለቱም ያተኮሩበት አንድ ሃሳብ/ቃል ምን ነበረ?
5. በቁ4 መሰረት የእግዚአብሄር ተቃውሞ ቤታችሁን ለምን ሰራችሁ ነው ወይ? ይህ ካልሆነስ የእግዚአብሄር ተቃውሞው ምን ነበረ?
6. በቁ5-6 ውስጥ ህዝቡ ምን እንዲያደርጉ ነው የሚያሳስባቸው? ከህይወት ልምምዳቸው እንዲያስተውሉ ከነገራቸው ነገሮች ጥቂቶቹን ዘርዝር፡፡
7. በእግዞአብሄር አመለካከት በልተው ያልጠገቡት፣ ጠጥተው ያረኩትና ለብሰው ያልሞቃቸው ምክንያት ለምንድነው?
8. የእግዚአብሄርን ቤት ለሚሰራበት ምቹ ጌዜና ሁኔታ ሊኖር ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ አስተሳሰብ ጋራ ምን ያህል ትላማማለህ? ለምን?

# ጥናት ሁለት (ሐጌ 1፡7-15)

የጥናት ዓላማ፡ በግልም ሆነ እንደ ቤተክርስትያን ለመንፈሳዊ መነቃቃት ዋነኛ ቅድመ ሁኔታ የሆነው ነገር የእግዚአብሄርን ቃል ሰምቶ መታዘዝ እንደሆነ ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡ ‹‹የእግዚአብሄርን ድምጽ…ሰሙ…ህዝቡም እግዚአብሄርን ፈሩ፡፡ ስለዚህ እግዚአብሄር…ከምርኮ የተረፈውን ህዝብ ሁሉ መንፈስ አነሳሳ፤ እነርሱም መጥተው የአምላካቸውን የእግዚአብሄር ጸባዖት ቤት መስራት ጀመሩ፡፡›› ሐጌ 1፡14

1. ሐጌ 1፡7-15 በአንድነት ይነበብ፡፡ በቁ7 እግዚአብሄር ህዝቡ እንዲያደርጉ ያሳሰባቸው ነገር ምንድነው? ይህ ማሳሰቢያ በቁ5 ላይም ተጠቅሷል፡፡ ለምንድነው እግዚአብሄር ደጋግሞ ይህንን ማለት ያስፈለገው ብለህ ታስባለህ?
2. በቁ8 ላይ ህዝቡ እንዲያደርጉ የሚጠየቁትን ሶስት ነገሮች በቅደም ተከተል ተናገር፡፡ በዚህ ክፍል መሰረት የቤቱ መሰራት የሚያስገኘው ነገር ምንድነው ይላል?
3. ቁ9-11ድን ስናነብ እግዚአብሄር ከህዝቡ የሚሮጥለትን ነገር እንዳያገኝ በተቃራኒ መንገድ እንደሚሰራ የሚጠቁሙን ሃሳቦች የትኞቹ ናቸው?
4. እግዚአብሄር ከህዝቡ ጥረት በተቃራኒ ሊሄድ ስለወሰነበት ምንንያት ክፍሉ ምን ይላል? ይህንን ስናይ ጌታ ስለቤቱ ስላለው አመለካከት ምን እንረዳለን? በዘመናችን በእነዚህ ሰዎች የደረሰው በእኛ ህይወት ሊገለጥ የሚችልበትን መንገድ ተወያዩበት፡፡
5. በቁ7-11ድን ስናይ የሰዎቹ አለመታዘዝ ከእነርሱ አልፎ ለሌሎች እርግማንን እንዳመጣ የሚያመለክቱን ጥቅሶች የትኞቹ ናቸው?
6. ቁ12ትን በማንበብ፣ ሐጌ የተናገረው ትንቤት ያስከተለው ውጤት ምን ነበረ? የሐጌ ትንቢት ተሰሚነት ስላገኘበት ምክንያት ክፍሉ ምን ይናገራል?
7. ቁ13 ‹‹እኔ ከእናንተ ጋራ ነኝ›› የሚለው መልዕክት ከመምጣቱ በፊት የቀደመው ምን ነበረ? ለምንድነው ይህ አባባል ከቁ12 መቅደም የማይችለው?
8. በቁ14 መሰረት እግዚአብሄር ከህዝቡ ጋራ መሆኑን ያረጋገጠው በምን መንገድ ነበረ? እርሱ ከእነርሱ ጋራ መሆኑስ በእነርሱ ውስጥ እንዴት ነው የተረጋገጠው?
9. የሰዎቹ መንፈስ የተነሳሳው ቃሉን ሰምተው ከታዘዙ በኋላ ነበረ፡፡ አንተስ ለእግዚአብሄርን ቃል ለመታዘዝ ምን ያህል ዝግጁ ነህ? በቃሉ ውስጥ የመንፈስ መነቃቃት አለና ከቃሉ ተጠጋ፡፡

# ጥናት ሶስት (ሐጌ 2፡1-9)

የጥናት ዓላማ፡ አገልግሎት እግዚአብሄር እንድንሰራ ያዘዘንን በታማኝነት የማከናወን ጉዳይ እንጂ ሌሎች ከሰሩትና ከሚሰሩት ጋራ ማወዳደር ወደ ትዕቢት ወይም ተስፋ ወደመቁረጥ ሊያደርሰን እንደሚችል ለመማር፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡ ‹‹የዚህ የአሁኑ ቤት ክብር ከቀድሞው ቤት ክብር ይበልጣል ይላል ሁሉን የሚገዛ እግዚአብሄር ጸባዖት፡፡›› ሐጌ 2፡9

1. ሐጌ 2፡1-9 ያለው ክፍል በአንድነት ይነበብ፡፡ ሐጌ ትንቢቱን በጀመረበትና በዚህ ትንቢት መሃል የነበተው የጊዜ ርቀት ምን ያህል ነበረ? ይህ ትንቢት ያተኮረው በማን ላይ ነበረ?
2. በቁ3 ውስጥ የእግዚአብሄር ሶስት ጥያቄዎች ምን ምን ነበሩ? ለጥያቄዎቹ የህዝቡ ምላሽ ምን ነበረ?
3. ለእነዚህ ሶስት ጥያቄዎች እግዚአብሄር የጠበቀው መልስ ምንድነው ብለህ ታስባለህ? ለምን ይህንን ለማለት እንደቻልክ አስረዳ፡፡
4. የማበረታቻ መልዕክት የመጣው ለማን ነበረ? የማበረታቻው ሁለገብ መሆን ለእኛ ምን ያስገነዝበናል?
5. በቁ4 ላይ ህዝቡ ለመስራት የተሰጣቸው ማበረታቻ ምን ነበረ? እኛስ በአገልግሎታችን ከእኛ ጋራ እንደሚሆን የተስፋ ቃል አለን ወይ? የትኛው ክፍል ውስጥ እንደሚገኝ ተናገር፡፡
6. በቁ6-9 ውስጥ እግዚአብሄር የሚገባላቸው የተስፋ ቃል ምን ነበረ? ይህንን ክፍል ስናይ እግዚአብሄር የራሱን ጥያቄ እየመለሰ ነው ማለት የሚያስችለን ምንድነው?
7. ወርቁም ሆነ ብሩ የእርሱ መሆኑን መናገር ለምን አስፈለገው ትላለህ?
8. የእነዚህን ሰዎች ፍርሃት ላይ የጣላቸው ነገር ምን ነበረ? አገልግሎትን ከሌሎች አገልግሎት ጋራ ማወዳደር ምን ችግር አለው ብለህ ትገምታለህ? የተሰጠህን አደራ በታማኝነት እየተወጣህ የጌታ ክብር በአገልግሎትህ በሙላት እንዲገኝ ብቻ ጌታን በመለመን ላይ ብቻ ትኩረት እያደረክ ተመላለስ፡፡

# ጥናት አራት (ሐጌ 2፡10-23)

የጥናት ዓላማ፡ በተቀደሰ ልብ፣ እግዚአብሄርን በመፍራትና በአክብሮት እስካላደረግነው ድረስ በቤቱ ውስጥ የምናከናውነውና የምናቀርበው መሥዋዕት በፊቱ ርኩስ ሆነው እንደሚታዩ ለማስጠንቀቅ፡፡

የምናሰላስለው ጥቅስ፡ ‹‹…ይህ ህዝብና ወገንም በፊቴ እንደዚሁ ነው ይላል እግዚአብሄር፤ የእጃቸው ሥራና የሚያቀርቡት ሁሉ የረከሰ ነው፡፡›› ሐጌ 2፡14

1. ሐጌ 2፡10-23 በአንድነት ይነበብ፡፡ በሐጌ 2፡2 ላይ ጥያቄ የቀረበው ለማን ነበረ? በዚህ ክፍልስ ተጠያቂው ማነው?
2. ቁ11-12 ላይ ካህናቱ የተጠየቁት ጥያቄ ምን ነበረ? መልስ እንዲመልሱ የተጠበቀባቸው ምንን አስመርኩዘው ነበረ?
3. በቁ13-14 ላይ ለካህናቱ የቀረበው ሁለተኛ ጥያቄ ምን የሚል ነበረ? ለዚህ ጥያቄ የካህናቱ መልስ ምን ነበረ?
4. እግዚአብሄር ከሁለቱ ጥያቄዎቹና ከካህናቱ መልስ የደረሰበት ማጠቃለያ ሃሳብ ምን ነበረ? ይህ ማጠቃለያ ሃሳብ ምን ማለቱ እንደሆነ አስረዳ፡፡
5. ቁ15-19 ላይ ነብዩ የሚናገረውን አጠቃላይ ሃሳቡ ምን ነበረ? በክፍሉ መሰረት በረከት ከህይወታቸወ የጠፋው ለምን ነበረ? የእጃቸውን ስራ መርገሙ በህዝቡ ልብ ያስከተለው ለውጥ ምን ነበረ?
6. እንዲያስታውሱትና እንዳይረሱት አጥብቆ የተናገራቸው የትኛውን ቀን ነው? ቀኑንስ እንዳይረሱት የፈለገበት ዋነኛው ምክንያት ለምን ነበረ?
7. የመጨረሻው የሐጌ ትንቢት ያተኮረው በማን ላይ ነበረ? በዘሩባቤል ላይ ብቻ ያተኮረበት ምክንያት ለምንድነው ብለህ ትገምታለህ? ለግሉ የተገባለት የተስፋ ቃል ምን ነበረ?
8. ቁ14ትን ስታነብ እግዚአብሄር ስለመስዋዕትታችን ዓይነት ስላለው አመለካከት ምን ታያለህ? መስዋዕትን ከማቅረብ በላይ መስዋዕትህን በተቀደሰ ልብ ስለማቅረብ ምን ያህል ጥንቃቄ ታደርጋለህ? እግዚአብሄር መስዋዕትን ብቻ ሳይሆን ልብንም አብሮ ስለሚመለከት ልትጠነቀቅ ይገባሃል፡፡